PDF Complete
Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 52
ADDIS ABABA 22nd July, 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፱/፪ሺ፮ ዓ.ም
የኢንቨስትመንት /ማሻሻያ/ አዋጅ ......................ገጽ ፯ሺ፬፻፶

CONTENTS

Proclamation No. 849/2014
Investment(Amendment) Proclamation ......... ............................................. Page 7450

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፱/፪ሺ፮

## የኢንቨስትመንት አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ስለኢንቨስትመንት የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፰፻፵፱/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጾች (፲፬)፣ (፲፭) እና (፲፯) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፲፬)፣ (፲፭) እና (፲፯) ተተክተዋል፡-

## PROCLAMATION No. 849/2014

## A PROCLAMATION TO AMEND THE INVESTMENT PROCLAMATION

WHEREAS it has become necessary to amend the Investment Proclamation No 769/2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Investment (Amendment) Proclamation No. 849/2014".

2. **Amendment**

The Investment Proclamation No. 769/2012 is hereby amended as follows:

1/ sub-articles (14), (15) and (17) of Article 2 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (14), (15) and (17):

፪/ በአዋጁ ውስጥ በማናቸውም ሥፍራ "ኤጀንሲ" የሚለው ስያሜ ተሠርዞ "ኮሚሽን" በሚለው ተተክቷል፡፡

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፯ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳፯ ተተክቷል:-

"፳፯. <u>የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት</u>

የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት የኢንቨስትመንት ቦርድን፣ ኮሚሽኑን እና በክልል ሕጎች የሚወሰኑ የክልል ኢንቨስትመንት አካላትን ያጠቃልላል፡፡"

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጾች (፭)፣ (፮) እና (፯) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፭)፣ (፮) እና (፯) ተተክተዋል:-

"፭/ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች በሚያቀርቧቸው ይግባኞች ላይ ይወስናል፤

፮/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሥራ ላይ ባለው ደንብ መሠረት ከሚፈቀደው የተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ ይፈቅዳል፤

፯/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ የተከለሉ የሥራ መስኮች ለውጭ ባለሀብቶችም ክፍት እንዲሆኑ ይፈቅዳል፡፡"

2/ any reference to the "Agency" appearing anywhere in the Proclamation is deleted and replaced by the "Commission";

3/ Article 27 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 27:

"27.<u>Investment Administration Organs</u>

The organs of investment administration shall comprise the Investment Board, the Commission and regional investment organs to be defined by the laws of the respective regions."

4/ sub-articles (5), (6) and (7) of Article 29 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (5), (6) and (7):

"5/ decide on appeals submitted to it by investors against decisions of the Commission;

6/ where necessary, authorize the granting of new or additional incentives other than what is provided for under the existing regulations;

7/ where necessary, and without prejudice to the provisions of Article 6 of this Proclamation, authorize the opening of investment areas for foreign investors, otherwise exclusively reserved for domestic investors."

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features

“፲፬/ ‘ኮሚሽን’ ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

፲፭/ ‘ኢንቨስትመንት ቦርድ’ ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

፲፯/ ‘የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና’ ማለት የኢንዱስትሪ እድገትን፣ የአካባቢ ብክለት ተፅኖ መቀነስን እና የከተሞች እድገትን በእቅድና በሥርዓት የመምራት ዓበይት ዓላማዎችን የያዘ ሆኖ እቅድን መሠረት አድርጎ እንደ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ውሃና የመሳሰሉ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶችና የተለያዩ አገልግሎቶች ተሟልተውለት እና ልዩ የማበረታቻ ዐቅድ ኖሮት፣ አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ወይም ተመጋጋቢነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎችን በስብስብ ለማልማት ወይም ሁለገብ ኢንዱስትሪዎችን ለማልማት የሚቋቋም ድንበር የተበጀለት አግባብ ባለው አካል የተሰየመ የተወሰነ ቦታ ሲሆን ልዩ የኢኮኖሚ ቀጠናን፣ የኢንዱስትሪ ፓርክን፣ የቴክኖሎጂ ፓርክን፣ የኤክስፖርት ማቀነባበሪያ ቀጠናን፣ ነፃ የንግድ ቀጠናን እና በኢንቨስትመንት ቦርድ የሚወሰኑ የመሳሰሉትን ይጨምራል፤”

“14/‘Commission’ means the Ethiopian Investment Commission to be established by regulation of the Council of Ministers;

15 /‘Investment Board’ means the Ethiopian Investment Board to be established by regulation of the Council of Ministers;

17/ ‘industrial development zone’ means an area with distinct boundary designated by the appropriate organ to develop identical, similar or interrelated industries together or to develop multifaceted industries, based on a planned fulfillment of infrastructures and various services such as road, electric power and water, and having special incentive schemes, with a broad view to achieving, planned and systematic, development of industries, mitigation of the impacts of environmental pollution and development of urban centers, and includes special economic zones, industrial parks, technology parks, export processing zones, free trade zones and the likes designated by the Investment Board;”

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



፭/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል:-

"፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢንዱስትሪ ቀጠና ልማት የሚካሄደው በፌደራል መንግሥት ወይም አስፈላጊነቱ ሲታመንበት በመንግሥትና በግል ባለሀብት በቅንጅት ወይም በግል ባለሀብቶች ይሆናል፡፡"

፮/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጾች (፩) እና (፪) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፩) እና (፪) ተተክተዋል:-

"፩/ የኢንቨስትመንት ቦርድ የኢንዱስትሪ ቀጠናዎች አስተዳደርንና ቁጥጥርን በበላይነት ይመራል፡፡

፪/ የኢንቨስትመንት ቦርድ በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጣው ደንብ ውስጥ የተቀመጡ ሥነ-ሥርዓቶችን፣ የፀደቁ የአገሪቱን የኢንቨስትመንት ዕቅዶች እና ስምምነቶች በመከተል ማናቸውም የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና እንዲጠብ ወይም እንዲሰፋ ማድረግን ይወስናል፡፡"

5/ sub-article (2) of Article 33 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub-article (2):

"2/ Without prejudice to the provisions of Article 6 of this Proclamation, industrial zone development shall be undertaken by the federal government or, where deemed necessary, by joint investment of the government and a private investor or by private investors."

6/ sub-articles (1) and (2) of Article 34 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (1) and (2):

"1/ The Investment Board shall oversee the administration and supervision of industrial development zones.

2/ The Investment Board shall, in conformity with the procedures provided for under this Proclamation and regulations issued hereunder and the approved investment plans and agreements of the country, decide the reduction or expansion of the boundaries of industrial development zones."

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.
Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



፯/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፬ ንዑስ አንቀጽ (፫) መጀመሪያ ላይ "በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪)የተመለከተው የውሳኔ ሃሳብ ሲጸድቅ በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ውስጥ በሊዝ የተያዘን ወይም በአዋሳኝ ቦታ ላይ የሚገኝን መሬት" የሚለው ሐረግ ተሠርዞ "የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና እንዲጠብ ወይም እንዲሰፋ መደረግ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሲወሰን በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናው ውስጥ በሊዝ የተያዘን ወይም በአዋሳኝ ቦታ ላይ የሚገኝን መሬት፣" በሚል አዲስ ሐረግ ተተክቷል፡፡

፰/ የአዋጁ አንቀጽ ፴፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተሠርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፪) እና (፫) ተተክተዋል:-

"፪/ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ስለሚሰየሙበት አሠራር፣ ስለሚመደቡበት መሥፈርቶች፣ ስለድንበራቸው አወሳሰን፣ በቀጠናዎች ውስጥ ስለሚሠማሩ ባለሀብቶች መብትና ግዴታዎች፣ ከመንግሥት ማግኘት ስለሚገባቸው ልዩ አገልግሎቶች አፈጻጸምና የቁጥጥር አሠራር፣ የሚያከናውኗቸው ግንባታዎች ስለሚፈጸሙበትና ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ሁኔታዎች፣ በዚህ አዋጅ ከሚያገኙት በተጨማሪነት ስለሚሰጧቸው ማበረታቻዎች እና በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎችን ለማስፈጸም አስፈላጊ ስለሆኑ ማናቸውም ጉዳዮች በኢንቨስትመንት ቦርድ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናሉ፡፡

7/ The phrase "Where the recommendation specified under sub-article (2) of this Article is approved a leasehold land within or adjacent to industrial development zones may be possessed by negotiation or decision for the purpose of:" appearing at the beginning of sub-article (3) of Article 34 of the Proclamation is deleted and replaced by the new phrase "Where the reduction or expansion of the boundary of an industrial zone is decided pursuant to sub-article (2) of this Article, a leasehold land within or adjacent to industrial development zones may be possessed by negotiation or decision for the purpose of:"

8/ sub-articles (2) and (3) of Article 35 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new sub-articles (2) and (3):

"2/ Measures concerning designation, allocation standard and boundary delimitation of industrial development zones, the rights and duties of investors engaged therein, the services expected from the government and supervision thereon, execution of construction activities and supervision thereon, incentives other than those granted under this Proclamation and the implementation of the provisions of this Part, shall be determined by directives of the Investment Board.

Your complimentary use period has ended. Thank you for using PDF Complete.

Click Here to upgrade to Unlimited Pages and Expanded Features



፫/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በሚወጣው የኢንቨስትመንት ቦርድ መመሪያ በተለየ አኳኋን የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።"

3/ Without prejudice to exceptions made by the provisions of this Part and directives of the Investment Board issued pursuant to sub-article (2) of this Article, other provisions of this Proclamation and regulations issued hereunder shall be applicable to industrial development zones."

3. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

3. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of July, 2014**

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**